# ደምብ

## MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅ ግብአቶች:** ABA-RB, EGG-RA, EGI-RA, JFF-RA, JHC, JHC-RA
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት:** Office of Teaching, Learning, and Schools

# በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ምርምር-ጥናት እና ሌላ መረጃ/ዳታ የመሰብሰብ ተግባሮች/አክቲቪቲዎች (Research and Other Data Collection Activities in Montgomery County Public Schools)

I. **ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጥናትና ምርምር እንዲሁም ሌሎች መረጃዎችን/ዳታ የመሰብሰብ እንቅስቃሴዎችን ተግባር የመገምገምና የማስተባበር ኃላፊነት ለመስጠት ይኼውም፡-

A. አሁን የሚሳተፉትን እና በፊት ተሳታፊ የሆኑትን ተማሪዎች፣ ወላጆቻቸውን/ሞግዚቶችን፣ አሁን በሥራ ላይ የሚገኙ ወይም የቀድሞ ሠራተኞችን እና ሌሎች MCPS-ስፖንሰር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ተሳታፊዎችን የብቻ/የግል ጉዳይ እንዳይጋለጥ ለመጠበቅ

B. የማስተማር ፕሮግራም መቋረጦችን ለመገደብ

C. በህዝባዊ ትምህርት ቤቶች የምርምር እና ሌላ መረጃ የማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ቴክኒካዊ ብቃትን፣ አዋጭነትን፣ እና ተገቢነትን ማረጋገጥ

II. **ቀደምት ዳራ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለማስተማር እና ለአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጠቃሚ የሆኑ ትምህርታዊ ምርምር እና መረጃ ማሰባሰብን ያበረታታል። የሆነ ሆኖ፥ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በስቴት እና የፌደራል ኤጀንሲዎች ግዴታ በተጣለበት በነዚህ የመረጃ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች እና በሌሎችም ተማሪዎች እና ሠራተኞች መሣተፍ እንደሚጠበቅባቸው ይገነዘባል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ክንውኖችን/እንቅስቃሴዎችን፣ ስልቶችና፣ መርሆዎችን ከፍተኛ ጥራትና ጥንካሬ ለመጠበቅ፥ ውስጣዊ ጥናትና ምርምር፣ ግምገማ እና ምዘናዎችን በ "Office of Teaching, Learning, and Schools - Shared Accountability (OTLS-SA)" አማካይነት ያስጠናል። በተመሣሣይ፥ MCPS ከትምህርት ቤቶች እና ከጽ/ቤቶች መረጃ ለማሰባሰብ የሚፈልጉ የውጭ ግለሰቦች እና ድርጅቶችም እንደዚሁ ከፍተኛ የጥናትና ምርምር ጥራት እንዲኖራቸው ያደርጋል። የተለዩ ሁኔታዎች ሲሆኑ፥ ለማስተማር ወይም ለአስተዳደራዊ የውሳኔ አሰጣጥ የሚያመች መረጃ ከመሰብሰብ ጋር የሚጣጣም ጥናት በማድረግ ኃላፊነታቸውን እና የሥራ ድርሻቸውን እንዲወጡ ይበልጥ መረጃዎችን/ዳታ ለመሰብሰብ ከዚህ በታች በ "section IV.C" ላይ የተዘረዘሩት አካላት የምህጻረቃል/አህጽሮተቃል መተግበሪያዎችን አሠራር እንዲጠቀሙ MCPS ይፈቅዳል።

III. **ትርጉም**

A. የምርምር/ሪሰርች እና ሌላ መረጃ የመሰብሰብ ተግባር ካላንደርማለት፥ በዚህ ደንብ አሠራር የተነደፈ

በካለንደር የተመዘገበ ምርምር/ሪሰርች እና ሌላ መረጃ/ዳታ የመሰብሰብ ተግባር ነው። ይህ ካላንደር በ OTLS-SA በይነመረብ ላይ ገኛል።

B. ውጫዊ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶችማለት ለትርፋማነት ወይም ትርፋማ ያልሆኑ የምርምር ድርጅቶች፣የአካባቢ/የስቴት/የፌደራል ኤጀንሲዎች፣ ብሔራዊ የጥናት ቡድኖች፣ ለዶክተርነት የሚያጠኑ እጩዎች፣ እና ሌሎች ለ MCPS ኦዲት እና ምርምር ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ የሚጠየቁና ምላሽ የሚሰጡ ውጫዊ ተመራማሪዎችንም ያካትታል።

C. መገልገያ መሣሪያዎች/ኢንስትሩመንትስማለት መረጃ/ዳታ ለመሰብሰብ የተነደፉ የኤሌክትሮኒክ ወይም በህትመት የተዘጋጁ ናቸው። በዚህ ብቻ የተገደበ ባይሆንም እነዚህየሚያካትቱት፥ የስምምነት ቅጾችን፣ የጥናት ቃለመጠይቆችን፣ የትኩረት ቡድን ወይም በስልክ ለማስተላለፍ/ለመጠየቅ የተዘጋጁ ጽሑፎችን፣ የምልከታ/የአስተውሎት መመሪያዎችን፣ እና ሌሎችም ምርምር ወይም ሌላ መረጃ/ዳታ የመሰብሰብ ተግባርን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ መገልገያዎችን ይሆናል።

D. የውስጥ አካላት ማለት የ MCPS ሠራተኞች፣ የ MCPS የሥራ ግብረኃይል፣ አማካሪ ቡድኖች፣ ወይም ኮሚቴዎች ናቸው።

የ "Montgomery County Council of Parent Teacher Associations (MCCPTA), Parent Teacher Associations (PTAs), እና Parent Teacher Student Associations (PTSAs) የውስጣዊ አካላት ባይሆኑም እንኳ፥ በ "Section IV.C." ያሉትን ድንጋጌዎች መከተል አለባቸው።

E. ምርምር/ሪሰርችማለት አስተማማኝ፣ ሊባዛ የሚችል፣ እና በጥቅሉ ማስፋፋት የሚቻል ግኝት፥ ስልታዊ የሆነ ምልከታ/አስተውሎት ወይም በሙከራ የተደገፉ ዲዛይኖች እና የሥራ መገልገያ መሣሪያዎች ናቸው። ምርምር በተለይም ለሳይንሳዊ ዕውቀት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ግኝቶችን የሚደግፉና ለማሠራጨት በቂ ድጋፍ የሚሰጡ ትንታኔዎችን እና ግኝቶችን ይጨምራል።

IV. **ቅደም ተከተሎች**

A. በውጫዊ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚደረግ ምርምር፣ እንዲሁም በ MCPS ሠራተኞች የሚቀርብ የማስትሬት ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ጥናት ወይም የዶክተርነት ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ ወይም የምርምር ፕሮጀክቶች

1. ውጫዊ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች፣ እንዲሁም የ MCPS ሠራተኞች ለማስትሬት ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ወይም ለዶክተርነት ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ ወይም ለምርምር ፕሮጀክቶች የሚደረግ ጥናት የሚከተለውን የምርምር ግምገማ ሒደት መጠቀም አለባቸው:-

    a) አመልካቾች ጥያቄ ሲያቀርቡ በ MCPS ድረገጽ ላይ የሚገኘውን ለምርምር ተግባር የኦንላይን ጥያቄ ማቅረቢያ (ORFARA) ሲስተም መጠቀም አለባቸው http://sharedaccountability.mcpsmd.org/ORFARA/App.php እና በ OTLS-SA የተጠየቀው የምርምር ጥናት በ MCPS ከሚጀመርበት ቀን ቢያንስ አራት ሣምንት ቀደም ብሎ አስፈላጊ የሆኑ አባሪዎችን ጭምር ማቅረብ አለባቸው። አባሪ የሚደረጉት ተዛማጅ የሆኑ የሥራ መሣሪያዎች (instruments)፣የተቋሙ ገምጋሚ ቦርድ(IRB) ያፀደቀው ውሣኔ፣ ከአሶሽየት ሱፐርኢንተንደንት እና/ወይም የምርምር ጥናቱ ከሚመለከተው ዳይሬክተር ድጋፍ የተጻፈ ደብዳቤ ወይም ኢ-ሜይል መካተት አለበት።

    b) የተጠየቀው የምርምር አካል የሆኑ መሥሪያ መሣሪያዎች በሙሉ ታይተው እስከሚጸድቁ ድረስ ምርምሩ ጥናቱ አይጀመርም።

c) አመልካቹ(ቿ) ቴክኒካዊ ብቃት ያለው የጥናት/የምርምር ስልት (methodology) ማሳየት(ቷ)ን እና እንቅስቃሴውም ለህዝብ ትምህርት ቤት ተገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ OTLS-SA ጥያቄውን ይገመግማል።

d) "The chief of Teaching, Learning, and Schools" ከፕሮጀክት ወጪ አንፃር፣ ከሚሰጠው ምላሽ፣ እና ለ MCPS ካለው ጠቀሜታ አንፃር ጥያቄውን ይገመግማል።

e) ጥናቱ እንዲቀጥል ለማድረግ፥ የ "OTLS-SA ወይም ተወካይ፣ እና የ chief of Teaching, Learning, and Schools" ፊርማዎች ያስፈልጋሉ። ጥያቄው ጠለቅ ያለ ግምገማ እንደሚያስፈልገው በአንዱ ወገን ከተወሰነ፣ መፈቀድ እንዳለበት፣ ወይም መፈቀድ እንደሌለበት እንዲወስን ወይም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ቀርቦ እስተያየት እንዲሰጥበት ወይም እንዲፀድቅ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እንዲወስን ይቀርባል።

2. ምርምር-ጥናት ለማድረግ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከኤፐሪል 1 በኋላ በ MCPS ተቀባይነት አይኖራቸውም። በ MCPS ተማሪዎችን የሚያካትት የምርምር ጥናት ከኤፐሪል 15 እስከ ሴፕተምበር 15 አይካሄድም። MCPS እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች-ቀኖችንም የመገደብ መብት አለው።

3. የሚከተሉት ተግባሮች/እንቅስቃሴዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም:-

a) የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ወይም የተመራቂ ኮርሶች፣ ሰሚናሮች፣ የሙያ፣ ወይም የስልጠና አውደጥናቶች ክሬዲት ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች የተነደፉ ተግባሮች/እንቅስቃሴዎች

b) የ MCPS ሠራተኛ ባልሆኑ ሰዎች የሚደረጉ የማስትሬት ዲግሪ ጥናቶች

c) በዚህ ደምብ ላይ ያሉትን መስፈርቶች በትክክል የማያሟሉ ተግባሮች/እንቅስቃሴዎች

d) በቺፍ ኦቭ ስታፍ፥ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የመማር፣ ማስተማር፣ እና ትምህርት ቤቶች ዋና ኃላፊ፣ እና የተሳትፎ፥ አዲስ ፈጠራ፥ እና የሥራ ሒደት ዋና ኃላፊ ካልተፈቀደ በስተቀር፥ የ MCPS የሥራ ባልደረባ በተመደበ(ች)በት በትምህርት ቤት ወይም በጽ/ቤት የሚካሄዱ የጥናት-የምርምር ተግባሮች።

4. በጥናት-በምርምር ፕሮጀክቶች ላይ የተማሪ እና የወላጅ/የሞግዚት ተሳትፎ በፈቃደኝነት የተመሠረተ ነው። በችፍ ኦቭ ስታፍ፣ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በተለይ ካልተገለጸ በስተቀር በ MCPS ሠራተኞች የሚደረገው ተሳትፎ በፈቃደኝነት ነው።

5. የምርምር አክቲቪቲው በዚህ መመሪያ ድንጋጌ መሠረት በይፋ የፀደቀ ካልሆነ፥ ከላይ እንደተገለጸው የ MCPS ሠራተኞች የምርምር ፈቃድ አይሰጡም ወይም በምርምር እንቅስቃሴው/አክቲቪቲው ላይ አይሳተፉም። በተመሣሣይ፥ በዚህ ደምብ ድንጋጌ መሠረት፥ የ MCPS ሠራተኞች ለስርጭት ያልተፈቀዱ መገልገያ መሣሪያዎችን ማስተላለፍ የለባቸውም።

6. ተመራማሪዎች/ሪሰርቸሮች የምርምር ፕሮጀክቱን ውጤት አንድ የተጠናቀቀ/የተሟላ የሪፖርት ቅጂ መስጠት ያለባቸው ሲሆን፥ከ MCPS ከተጠየቀ፥ከ 25 ገጽ ያልበለጠ የምርምር ጥናት ማጠቃለያ ሪፖርት መስጠት አለባቸው። ተመራማሪዎች ለማናቸውም እነዚህ ሪፖርቶች፣

ውጤቶች/ምርቶች፣ ወይም የምርምር ማጠቃለያዎች ከ MCPS ኢያስከፍሉም፥ እና ሪፖርቱ በተጠናቀቀ ወይም ምርቱ/ውጤቱ በተዘጋጀ በ30 ቀናች ውስጥ (ቀዳሚው የትኛውም ቢሆን) መስጠት ይኖርባቸዋል።

B. ከ MCPS ውጭ ከሆኑ አካላት ጋር መረጃ/ዳታ መለዋወጥ

በኮንትራት ወይም ከ MCPS ጋር ባለ ስምምነት መሠረት የሚሠራ ማንኛውም አካል ስለ መረጃ/ዳታ ልውውጥ የስምምነት ውል ማድረግ አለበት። የሠራተኛ እና የተማሪ መረጃን በሚመለከት የሚከናወኑ የኮንትራት ስምምነቶች በጠቅላላ የፌደራል እና የስቴት መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው።

አንድ አካል ከ MCPS ጋር የመረጃ/ዳታ ልውውጥ በማድረግ የሚሠራ ኮንትራት ወይም ስምምነት ካለው ሌላ አካል ጋር ከተዋሃደ፣ ቀጣዩ አካል በፊት በተደረገው ስምምነት ላይ ያሉትን ግዴታዎች የማክበር ሃላፊነት አለበት።

C. በ MCPS የውስጥ አካላት አማካይነት ስለሚሰበሰብ መረጃ/ዳታ

1. በ "Section IV.D.," ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር ከትምህርት ቤት ወይም ከጽ/ቤት ሠራተኞች መረጃ ለመሰብሰብ የሚጠይቁ የ MCPS ሠራተኞች፣ የ MCPS የሥራ ግብረኃይል፣ አማካሪ ቡድኖች ወይም ኮሚቴዎች፣ እና MCCPTA፣ PTAs፣ እና PTSAs የፕሮፖዛል ናሬቲቭ ወይም ኤክስፐርመንታል ዲዛይን ማቅረብ አይጠበቅባቸውም ነገር ግን ከዚህ በታች ያሉትን ደረጃዎች/ስቴፖች መከተል አለባቸው፡-

    a) አመልካቾች በ MCPS ቅጽ 226-21 የተሞላ ጥያቄ "Request for an Internal Data Collection Activity" እና አስፈላጊ አባሪዎችን፣ ጥያቄ የሚቀርብላቸው መልስ ሰጪዎች/ሪስፖንደንቶችን ዝርዝር እና የመሥሪያ መሣሪያዎችን (instrument) ቅጂ፣ ለ OTLS-SA ቢያንስ የተጠየቀው መረጃ የማሰባሰብ ስራ በ MCPS ከመጀመሩ ሁለት ሣምንት አስቀድሞ ማቅረብ አለባቸው።

    b) OTLS-SA ጥያቄው የቀረበበትን ጊዜ፣ አግባብነት ካላቸው የ MCPS ደምቦች ጋር የማይጣረስ ስለመሆኑ፣ እና ስለ ተጠያቂነት ኃላፊነት በሚመለከት የቀረበውን ጥያቄ ከገመገመ በኋላ ለ "chief of Teaching, Learning, and Schools and the chief of Engagement, Innovation, and Operations" አስተያየት ያቀርባል።

    c) "The chief of Teaching, Learning, and Schools እና The chief of Engagement, Innovation, and Operations ከ OTLS-SA's በቀረበው ጥያቄና አስተያየት መሠረት ድርጊቱ/አክቲቪቲው በህዝብ ትምህርት ቤት አውድ ተገቢነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ይገመግማሉ።

    d) ጥናቱ እንዲጀመር-እንዲቀጥል ለማድረግ የ "chief of Teaching, Learning, and Schools and the chief of Engagement, Innovation, and Operations" ፊርማዎች ያስፈልጋሉ። ጥያቄው በትኩረት መገምገም እንዳለበት ማንኛውም አካል ከወሰነ፥ ጥያቄው እንዲፀድቅ ወይም እንዳይፀድቅ ወይም ለቦርድ ቀርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት ወይም ውሳኔ እንዲያገኝ ለማድረግ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ ይቀርባል።

2. የሚከተሉት ገደቦች ተግባራዊ ይሆናሉ፡-

a) በመልስ ሰጪው(ዋ) ላይ የሚኖረው ጫና አነስተኛ መሆን አለበት፣ እና የሚቀርቡትም ጥያቄዎች ውስን መሆን አለባቸው (ይኼ ማለት፤ በግምት ከአምስት እስከ ሰባት ጥያቄዎች አግባብነት ይኖረዋል)።

b) አመልካቾችየምርምር እና ሌላ መረጃ/ዳታ አሰባሰብ ተግባር-አክቲቪቲ ካለንዳር/Calendar of Research and Other Data Collection Activitiesበ OTLS-SA በይነመረብ ላይ ፖስት የተደረገውን መመልከት አለባቸው፥ እና ቀደም ሲል የተያዘ እቅድ ነው በማለት በአንድ ተመሣሣይ ጊዜ ወይም ለምዘና ወይም ለዳሰሳ ዝግ በተደረጉባቸው ቀኖች መረጃ/ዳታ የመሰብሰብ ተግባሮችን-አክቲቪቲዎችን ማስወገድ አለባቸው።

c) በ "section IV.A.4." ላይ ባለው ድንጋጌ መሠረት፥ በመረጃ ማሰባሰብ ተግባር/አክቲቪቲ ላይ የመልስ ሰጪ/ሪስፖንደንት ተሳትፎ የሚሆነው በፈቃደኝነት ነው።

D. መረጃ/ዳታ የማሰባሰብ ተግባሮች/እንቅስቃሴዎች በዚህ ደምብ የሚወሰኑ አይሆኑም።

1. ከተለያዩ ክፍሎች/ዩኒቶች የሠራተኞችን መረጃ/ዳታ ለማሰባሰብ የሚፈልጉ የሠራተኛ ማህበራት ተግባሮች/አክቲቪቲዎች (ለምሳሌ፡- የዳሰሳ ጥናት) ከማህበራቱ መሪዎች/ስራ አስኪያጅ ባልደረቦች/የዋና ሥራ አስኪያጅ የትብብር ኮሚቴ (ADC) ፈቃድ/ይሁንታ ማግኘት አለባቸው።

2. ከወላጅ/ከሞግዚት በቀጥታ መረጃ ለመሰብሰብ የሚጠይቁ የ MCCPTA፣ PTAs፣ እና PTSAs አባላት የዚህ ደምብ ድንጋጌ አይጠበቅባቸውም።

a) በወላጆች/ሞግዚቶች፣ MCCPTA፣ PTAs፣ እና PTSAs አማካይነት የሚካሄዱ ከተማሪዎች መረጃ የሚፈልጉ የዳታ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች/ተግባሮች አይፈቀዱም።

b) ከ MCPS ሠራተኞች መረጃ/ዳታ የማሰባሰብ ተግባሮች/አክቲቪቲዎች በዚህ ደንብ ተመርኩዞ ሊፈቀዱ ይችላል፤ የሆነ ሆኖ፥ በተማሪ ላይ ወይም በሥራ ባልደረባ የተለየ ድርጊት ላይ ያነጣጠረ መረጃ/ዳታ የመሰብሰብ ተግባሮች/አክቲቪቲዎች አይፈቀዱም።

3. ይህ መመሪያ-ደምብ ለሚከተሉት ተግባራዊ አይሆንም፡-

a) መረጃ/ዳታ የመሰብሰብ አሰራር፣ ቴስቶች፣ ወይም ሌላ የተማሪዎቻቸውን የትምህርት አቋም እና እድገት ለመመዘን በአስተማሪዎች የተዘጋጁና ጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ/ዳታ ተደራሽነት ቅጾች

b) ከማስተማር ጋር ለተገናኙ ዓላማዎች ተፈላጊ የሆኑ የመረጃ/ዳታ ተደራሽነት ያላቸውና የሚጠቀሙ አስተማሪዎች

c) የመሰብሰብ፣ ተደራሽነት ያላቸው፣ ወይም ሃላፊነታቸውን ለመወጣት እና ሥራቸውን ለማከናወን በተፈጥሮ የሚያስፈልጉና የተለመዱ መረጃዎችን/ዳታዎችን የሚጠቀሙ የትምህርት ቤት አመራር ቡድኖች፥ በተጨማሪም፡-

(1) በትምህርት ቤቶቻቸው ተማሪዎችን መረጃ/ዳታ የሚጠይቁ፣ በትምህርት ቤቶቻቸው ምድብ ዙርያ የሚገኙ ማህበረሰብ አባላት፣ ወይም በትምህርት ቤቶቻቸው የሚገኙ ሠራተኞች

(2) በቀጥታ ከሚቆጣጠሯቸው ሠራተኞች መረጃ/ዳታ መጠየቅ

V. **ምስጢር የመጠበቅ እና የመረጃ/ዳታ ደህንነት መስፈርቶች**

A. የሁሉም የምርምርና ጥናት ተሳታፊዎች ማንነት እና መረጃ ግላዊ ገመናን የመጠበቅ ህግ ከማክበር አኳያ FERPA ጭምር በምስጢር መጠበቅ አለባቸው።

B. በተመራማሪው(ዋ)/አጥኚው(ዋ) ወይም በማናቸውም የርሱ(ሷ) ሠራተኛ አማካይነት ከ MCPS ውጪ ለሆነ ማንም ግለሰብ ወይም አካል—ማንኛውም ብሔራዊ ጥናት—ተለይቶ ያልታወቀ የ MCPS የሥራ ባልደረባ፣ ትምህርት ቤት፣ ወይም ዲስትሪክት ጭምር በቅድሚያ ተገምግሞ ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ካልተፈቀደ በስተቀር ምንም አይነት መረጃ/ዳታ ወይም የምርምር-ጥናት ግኝቶችን ለማጋራት አይፈቀድም።

C. የተገኙት የጥናት-ምርምር ሪኮርዶች እና የመስሪያ መሣሪያዎች ያልተፈቀደ ተደራሽነትን፣ ውድመት፣ የአጠቃቀም ለውጥ ማድረግን፣ ወይም ይፋ ማድረግን ለመከላከል በአግባብ መያዝ እና መቀመጥ አለባቸው።

D. አመልካቾች ስለ ምርምር-ጥናት ተሳታፊዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ወይም ዲስትሪክት በዚህ መመሪያ ድንጋጌ መሠረት ካልሆነ ወይም በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር ለማስተዋወቅ/አድቨርታይዝ ማድረግ፣ ወይም የተማሪን መረጃ መሸጥ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት/ይፋ ማድረግ አይፈቀድም።

E. የጥናት-ምርምር ፕሮጀክትን በሚመለከት ማንኛውም የታወቀ ወይም የተጠረጠረ የመረጃ/ዳታ ደህንነት እና ምስጢራዊነትን መጣስ በፍጥነት ወደ OSA ሪፖርት መደረግ አለበት።

F. ፕሮጀክቱ ሲያበቃ/ሲቋረጥ የጥናት-ምርምር ሪኮርዶቹ እንዲወገዱ መደረግ አለበት።

G. ዳሰሳዎቹ "PPRA" እና የ "Maryland Student Data Privacy Act of 2015" የሚያከብሩና የማይጣረሱ መሆን አለባቸው።

**ተዛማጅ ምንጮች:** Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA), 20 U.S.C. §1232g, 34 CFR Part 99; Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA), 20 U.S.C. §1232h, 34 CFR Part 98, (2000 and Supp. IV 2004); Maryland Student Data Privacy Act of 2015, Annotated Code of Maryland, Education Article, §4-131

**ስለ ደምቡ ታሪክ፡-** የቀድሞው ደምብ/Regulation 340-2፣ ጃኑወሪ 5/1973 ሲሆን፥ ጁላይ1984 ተሻሽሏል፥ ኖቨምበር 19/1991ተሻሽሏል፥ ጃኑወሪ 10/2003 ተሻሽሏል፥ ዲሰምበር 14/2011 ተሻሽሏል፥ ማርች 12/2013 ተሻሽሏል፥ ዲሰምበር 6/2013 ክለሳ ተደርጓል፥ ኦክቶበር 22/2014 ማሻሻያ ተደርጎበታል፥ ኖቨምበር 18/2014 ተሻሽሏል፥ 27/2016 ክለሳ ተደርጓል፥ ማርች 5/2021 ክለሳ ተደርጓል።